የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፷
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 60
ADDIS ABABA 4th September, 2007

ማ ው ጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፵፱/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

የማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅን ማፅደቂያ አዋጅ…. ገጽ ፫ሺ፰፻፹፰

CONTENTS

Proclamation No. 549/2007

Maritime Sector Administration Proclamation …. Page 3888

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፵፱/፲፱፻፺፱

## የማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ

የተቀላጠፈ የማሪታይም ዘርፍ አገልግሎት ለአገር ልማትና ብልጽግና እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ በተፋጠነ ሁኔታ ተሻሽሎና በተቀናጀ አደረጃጀት ተስፋፍቶ የበለጠና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በዘመናዊ የአሠራር ቴክኒክ ዘዴዎች በመጠቀም የደረቅ ወደቦችን፣ የባሕር ማመላለሻንና መልቲ ሞዳል ትራንስፖ ርት አገልግሎትን መጠቀም እንዲቻል ለማድረግ፣ መርከ ቦችን፣ የባሕር ጉዞዎችንና ሌሎች የማሪታይም ዘርፍ አገልግሎቶችን በሚገባ መምራትና መቆጣጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣ እንዲሁም የአገር ውስጥ የውሃ ኃብትን ለበለጠ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲውል ለማድረግ፣እና

በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ሥር ተበታትነው ያሉትን ተግባራት በአንድ ላይ በማሰባሰብ በማሪታይም ዘርፍ የሚከሰቱ ችግሮችን ተከታትሎ መፍትሔ የሚሰጥ፣ በአለም ዓቀፍ ባሕር ነክ ስምምነቶች ላይ በመመስረት አገራችን ግዴታዋን እንድትወጣ እና ልታገኝ የሚገባትንም ጥቅሞች ተከታትሎ በባለቤትነት የሚያስፈጽም ለትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር በቀጥታ ተጠሪ የሆነ መንግሥታዊ አካል ማቋቋም በማስፈለጉ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ /፩/መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO.549/2007.

## MARITIME SECTOR ADMINISTRATION PROCLAMATION

WHEREAS, it is imperative to improve and expand the maritime sector in an organized manner to provide an enhanced and smooth service, considering the crucial importance of existence of efficient maritime sector for a country's development and prosperity;

WHEREAS, it is essential to use modern means and techniques to administer dry ports , marine transport multimodal transport services and regulate vessels and marine transport and other maritime services, and to make use of inland water ways for transportation, and

WHEREAS, it is necessary to establish a Government body reporting directly to Ministry of Transport and Communication, which assumes maritime-related duties currently carried out by various Government bodies to date; becomes responsible for analyses and work out of maritime related issues; and is responsible for follow up and execution of obligations and rights of our country under international maritime conventions ;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows;

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩/ አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፭፻፵፱/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

### ፪/ ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም እንዲሰጠው ካላስገደደ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው።

፪/ "ባለሥልጣን" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ መሠረት የተቋቋመው የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ነው።

፫/ "የባሕር ማመላለሻ አገልግሎት" ማለት በባሕር መንገደኛን፤ ጭነትን ወይም ፖስታን የማመላለስ አገልግሎት ነው፤

፬/ "ወደብ" ማለት ዕቃዎች ወደ ውጪ ሃገር የሚጫኑበትና ወደ ሃገር ውስጥ ሲገቡም የሚራገፉበት ቦታ ተብሎ አግባብነት ባለው ሕግ ተደንግጎ የተከለለ የጉምሩክ መ/ቤት ያለበት የባሕር ወይም ደረቅ ወደብ ሲሆን፤ በዚህ ክልል ውስጥና በአዋሳኙ ለዚሁ አገልግሎት የሚውሉትን ሕንፃዎች፤ ድርጅቶችና መሣሪያዎች ይጨምራል፤

፭/ "የወደብ አገልግሎት" ማለት በወደብ ውስጥ ለሐመር መቆሚያ መስጠትን፣ ሐመር መጎተትን፣ የሐመር አገልግሎት መስጠትን፣ ዕቃዎችን በሐመር ላይ መጫንና ማራገፍን፣ ለጭነት ተሽከርካሪዎች መቆሚያ መስጠትን፤ የጭነት ተሽከርካሪዎችን መጎተትን፤ ዕቃዎችን በወደብ ውስጥ በጭነት ተሽከርካሪዎች ላይ መጫንና ማራገፍን፤ ወዘተ በወደብ ክልል ውስጥ ዕቃን ማጓጓዝን፤ የእሳት አደጋ አገልግሎት መስጠትን፤ የመጋዘን አገልግሎት መስጠትንና የመሳሰሉትን ይጨምራል፤

፮/ "ባሕረኛ" ማለት በሐመር ላይ ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ እንዲሠራ የተደረገ ማንኛውም ሰው ሲሆን አዛዡንና ለማጆችን ይጨምራል፤

## Part One
## General

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as “Maritime Sector Administration Proclamation No. 549/2007”

### 2. Definition

Unless the context provides otherwise the definition of words in this Proclamation is as follows:

1/ “Minister” or “Ministry” shall mean the Minister or Ministry of Transport and Communication respectively.

2/ “Authority” shall mean the Maritime Affairs Authority established in accordance with Article 3 of this Proclamation.

3/ “Marine Transport Service” shall mean the carriage by sea of passengers, goods, or mail.

4/ “Port” shall mean any area designated by the law as a place where goods are loaded or unloaded in which customs office is situated and any buildings, installations and equipment or adjacent to any sea or dry port used for these purpose.

5/ “port service” shall mean the berthing and un berthing of vessels in a port, towage and pilot age of vessels, loading and unloading of goods on or from vessels; embarkation and disembarkation of passengers on or from vessels, transport of goods within a port; providing parking services for freight trucks, towing freight trucks, loading and unloading of goods on such trucks etc in sea ports or dry ports, fire fighting service, ship-chandelling, ware-housing and other similar services;

6/ “Seafarer” shall mean any person, including masters and apprentices, employed or assigned to work on board a vessel.

፯/ "ለባሕር ጉዞ ብቁነት" ማለት አንድ ሐመር በአሠራሩ፤ በአጫጫን ዕቅዱ፤ በስንቁና በባሕረኞቹ ብቁና የተሟላ ሆኖ የተመደበበትን ተግባር ለማከናወን የሚችል መሆኑ በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ነው፤

፰/ "ሐመር" ማለት በውሃ ላይ ለመጓጓዝ የሚያገለግል ማንኛውም ዓይነት መርከብ፤ ጀልባ፤ ታንኳ ወይም ሳንቡቃ ነው።

፱/ "የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥራ" ማለት ወጥ በሆነ የትራንስፖርት ውል መሠረት ቢያንስ በሁለት የተለያዩ የማጓጓዣ አይነቶች በመጠቀም በክፍያ ዕቃን ከአንድ የተወሰነ ቦታ ተረክቦ በማጓጓዝ ሌላ አገር ውስጥ ማስረከብን የሙያ ሥራ አድርጎ ጥቅም ለማግኘት ሲባል የሚሰራ ሥራ ማለት ነው።

## ክፍል ሁለት
## የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን

**፫. መቋቋም፡-**

ከዚህ በታች "ባለሥልጣን" እየተባለ የሚጠቀሰው የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ተጠሪነቱ ለትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር የሆነ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

**፬. ዋና መሥሪያ ቤት፡-**

የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን በማናቸውም ቦታ ሊያቋቁም ይችላል።

**፭. ዓላማዎች፡-**

ባለሥልጣኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

፩/ በገቢና ወጭ፣ ንግድ ኮሪደሮች የሚካሄደው የገቢና ወጪ ዕቃዎች እንቅስቃሴ ኢኮኖሚያዊ መሆኑን መቆጣጠር፣ በዕቅድ እንዲመራ ማድረግና ማስተባበር፣

፪/ የገቢና የወጪ ዕቃዎች የትራንዚት ጊዜ እንዲያጥርና ወጪው እንዲቀንስ፣ ዕቃዎች በወደቦች ላይ ጉዳት እንዳይደርስባቸው የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው እንዲሰሩ ማስተባበርና መምራት፣

7/ “Sea worthiness” shall mean the fitness in construction, stowage plans, provisions and manning.

8/ “Vessel” shall mean kind of ship, boat, watercraft or dhow used for marine transport.

9/ “Multimodal Transport” shall mean the carriage of goods by at least two different modes of transport, on the basis of a multimodal transport contract, from a place at which the goods are taken in charge by the multimodal transport operator to another place designated for delivery, situated in a different country.

## Part Two
## Maritime Affairs Authority

**3. Establishment:-**

There is hereby established a Maritime Affaires Authority (hereinafter the “Authority”) as an autonomous public authority having its own judicial personality.

**4. Principal office:-**

The Authority shall have its principal office in Addis Ababa and may establish branch offices elsewhere.

**5. Objectives:-**

The purposes for which the Authority is established are as follows:-

1/ ensure that the transport operations and movement of goods in import and export of the country are economical; plan, coordinate and enforce such operation;

2/ reduce the transit time of import export of goods, and coordinate the concerned Government bodies to care for goods at port.

፫/ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት፣ የባሕርና የአገር ውስጥ ውሃ ትራንስፖርት በማንኛውም ረገድ የሚያድጉበትን መንገድ መፈለግ። የባሕር ማመላለሻ አገልግሎት ከፍተኛ ደኅንነት እንዲኖረው ማረጋገጥ፤ በአገሪቱ የዳበረና ቀጣይነት ያለው የማሪታይም ዘርፍ ክህሎት እንዲኖር ማድረግ፤

፬/ ከአለም ዓቀፍ የማሪታይም ዘርፍ ስምምነቶች ጋር በተያያዘ አገሪቷ መፈጸም ያለባትን ግዴታና ልታገኝ የሚገባትን ጥቅም ተከታትሎ ማስፈጸም።

3/ seek ways and means for the promotion and development of multimodal transport, marine transport, in-land water transport and ensure the availability of uninterrupted resource of skilled man power in the maritime sector for the Country .

4/ to implement obligations and rights of Ethiopia under international maritime conventions.

## ፮. ሥልጣንና ተግባር፡-

ባለሥልጣኑ የተሰጡትን ዓላማዎች ከግቡ ለማድረስ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

፩/ በገቢና ወጪ ንግድ ኮሪደሮች የሚካሄደውን የገቢና ወጪ እቃዎች እንቅስቃሴ የአገሪቷን የገቢና ወጪ ዕቃዎች እንቅስቅሴ ኢኮኖሚያዊነትና ቀልጣፋነት ማረጋገጥ፣ መቆጣጠር፣ ማስተባበርና ለችግሮች አፋጣኝ መፍትሔ መስጠት

፪/ የገቢና ወጪ ዕቃዎች የትራንዚት ጊዜ እንዲያጥር የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው እንዲሰሩ መምራት፣ የባሕር ወደብ አጠቃቀምን በተመለከተ ለሚከሰቱ ችግሮች ተከታትሎ መፍትሔ መስጠት፣ መደራደር፣

፫/ በባሕር ወደቦች የራሱ የመርከብ መጠጊያ እንዲኖረው መጣር፣ የደረቅ ወደብ ግንባታና አገልግሎት ማስፋፋት፤ የገቢና ወጪ ዕቃዎች የትራንዚት የመርከብና ሌሎች ጭነቶች ዋጋ ለመደራደር የሚያስችል ክህሎት ማዳበር፤

፬/ ብሔራዊ የንግድ መርከብ እንዲጎለብት መጣር፣ አሰራሩን መቆጣጠር፤ ለባሕርና ለሃገር ውስጥ ውሃዎች ማመላለሻ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የሥራ ፈቃድ መስጠትና መቆጣጠር፡

፭/ የማንኛውንም ሐመር ሥራ፤ ይዞታ፤ አገልግሎት ላይ ማዋል፤ ሽያጭና ግዥ መቆጣጠር፤ ለባሕረኞች፤ ለሌሎች በሐመር ላይ ለሚሠሩ ሰዎች አስፈላጊውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠትና ማደስ፤

## 6. Powers and Duties of the Authority

The Authority shall have all the powers and duties to:

1. ensure that the import and export process and movement of goods is economical and efficient; supervise, coordinate and render timely solutions to problems arising in the course of these operations;

2. direct and coordinate efforts of the respective Government bodies to minimize the transit time of import and export goods; analyze and solve problems arising from the use of sea ports and negotiate on such matters;

3. ensure the availability of its own berth at sea ports; develop the construction and expansion of service of dry ports, develop skills in negotiation of cost of transit, shipping of goods and other freight services in the course of import and export operation;

4. strive for the strengthening of the national shipping carriers, supervising its activities, issue license and supervise bodies and persons engaged in sea and inland waterways transportation services;

5. regulate, the manufacture, possession, use, sale and purchase of any vessel, license and control seafarers, pilots and other persons working on board a vessel;

፮/ ማናቸውንም የደረቅ ወደብ አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎች ወይም መገልገያዎች መመርመርና መፍቀድ፤ የደረቅ ወደብ አገልግሎት፣ የሃገር ውስጥ ጉምሩክ ማስተላለፊያ ቦታዎችን አገልግሎቶች መቆጣጠር፤

፯/ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥራ መሰማራት ለሚፈልጉ ፈቃድ መስጠት፣ ማደስና መቆጣጠር

፰/ የደረቅ ወደቦችን፣ የወደብ ዕቃ አስተላላፊዎችን፣ የመርከብ ወኪሎችንና የጉምሩክ አስተላላፊነትን ሥራ መቆጣጠር፣ ዝርዝር መመሪያዎችን ማውጣት፣ ሥራቸውን ማስተባበር፣ አቅማቸውን ማጐልበት፤

፱/ ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ ዓለም አቀፍ የማሪታይምናትራንዚት አገልግሎት ስምምነቶች መደራደር፣ ደንቦች እንዲወጡ ወይም እንዲተገበሩ ማድረግ፣ አፈጻጸማቸውን መከታተል፣

፲/ በማሪታይም ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥ የግል ባለኃብቶች የተደራጀና የተቀናጀ ተሳትፎ እንዲጐለብት ማገዝ፣ በማሪታይም ዘርፍ የሚደራጁ ማህበራትን ሥራ መቆጣጠር፤ የማሪታይም ዘርፍን የሚመለከቱ የንግድ መረጃዎችን በትንታኔ በማስደገፍ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ፤

፲፩/ በደረቅ ወደብ፣ አገልግሎት የተሰማሩ ድርጅቶች ለሚሰጡት ግልጋሎት የሚያስከፍሉትን ዋጋ ወይም ታሪፍ ማስወሰን፤ መንገደኞች፤ ዕቃዎችና ፖስታዎች በሐመር የሚጓጓዙበትን ሁኔታ መወሰንና መቆጣጠር፤

፲፪/ የደረቅ ወደቦችንና ሌሎችንም ውሃ ትራንስፖርት ነክ ጉዳዮችና ተግባሮች በማጥናት ፕላንና ፕሮግራም ማዘጋጀት፤ በሚፈቀደው ፕሮግራም መሠረት ደረቅ ወደቦችና ሌሎችንም የሐመር መገልገያዎች ማቋቋም፣ማሻሻልና መጠገን፤

፲፫/ ደኅንነቱ የተጠበቀ፤ በቂ እና የተሟላ የደረቅ ወደብ የባሕር ማመላለሻና የወደብ አገልግሎቶች መኖራቸውን ማረጋገጥ፤ አስፈላጊው የባሕርና የየብስ መድን እንዲኖር ማድረግ፤

፲፬/ የወደብና የሐመር መዛግብትን መያዝ፤ ማናቸውንም ሐመር ከነመብቱ መመዝገብ፤ ለሐመር የመለያ ምልክት መስጠት፤ የሐመር ስምን መፍቀድ፤ የባሕር ጉዞ ብቁነት የምስክር ወረቀት መስጠት፤ ሐመር የሚሠራበትን፤ የሚውልበትን ተግባር የሚጠበቅበትን፤ የሚታደስበትንና የሚጠገንበትን ሁኔታ መወሰንና መቆጣጠር፤

6/ inspect, license and regulate all dry port and vessel services and facilities, the services at custom check points;

7/ issue license to persons desiring to engage in multi modal transport business, renew such license and supervise their operation;

8/ regulate and supervise dry ports, freight forwarders, ship agents, and the operation of customs clearing, to issue detailed directives, coordinate their tasks, and improve their capacity;

9/ negotiate, with the approval of the Ministry, international maritime and transit services, issues implementation regulations and follow up their execution;

10/ support the increased private organized participation in the organized manner in the maritime service sector, supervise the activities of associations organized in the maritime sector, disseminate properly analyzed trade information regarding the maritime sector to end users.

11/ recommend tariffs to be charged at dry ports, for the services they render; regulate the conditions under which passengers, goods and mail may be-transported in vessels;

12/ conduct research and prepare plans and programs for dry ports and other projects relating to maritime transport construction, improve and maintain dry ports and other facilities for the use in accordance with the authorized programs ;

13/ ensure the availability of safe and adequate marine transport and dry port services; require the provision of necessary marine and surface transport insurance;

14/ maintain port and vessel records; register all vessels and any rights relating thereto, issue registration marks to vessels; approve vessel christening; inspect and issue seaworthiness certificates; specify the type of services for which vessels are to be used; preserve and regulate conditions as to the construction assignment, maintenance and repair of vessels;

፲፭/ የባሕር መበከልን ወይም መቆሸሽን መቆጣጠር፤ ከሌሎች ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ለሃገር ውስጥ ውሃ ማመላለሻ የተከለከሉ፤ አደገኛ ወይም ባለገደብ ቦታዎች መከለልና ማሳወቅ፤

፲፮/ ማንኛውም ሐመር ቢጠፋ ወይም በባሕር ላይ እንዳለ አደጋ በደረሰበት ጊዜ የፍለጋ፤ የማዳንና የአስቸኳይ ዕርዳታ ተግባሮችን ማስተባበር፤ የሐመር አደጋን መመርመር፤ የአደጋ ምርመራ ሪፖርት አዘጋጅቶ ማውጣት፤

፲፯/ የባሕር ትራንስፖርት ሙያ ማስተማሪያ ተቋማት፤ የሐመር ሥራ፤ ማደሻና መጠገኛ ድርጅቶች፤ እንዲሁም ሌሎች ለሐመር አገልግሎት የሚውሉ ክፍሎች እንዲቋቋሙ ማድረግ፤ ደረጃቸውን መመርመርና መወሰን፤ የችሎታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት

፲፰/ ባለሥልጣኑ በወደብ ክልል ውስጥና እንዲሁም ለባሕር ጉዞ ለሚያበረክተው ማናቸውም አገልግሎቶች ተገቢውን ዋጋ፤ ኪራይ ወይም ሌላ ክፍያ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በማቅረብ አፀድቆ ማስከፈል።

፲፱/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ረቂቅ መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ የማቅረብ፣ በየወቅቱ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ በግልጽ እንዲያውቁት ማድረግ።

፳/ ውል መግባት፤ መክሰስና መከሰስ፤ ክርክሮችን በግልግል መጨረስና ለሥራው እንደሚያስፈልገው ማንኛውንም ዓይነት ንብረት መግዛት፤ መሸጥ፤ ባለቤት መሆን፤ መከራየት ወይም ማከራየት፤

## ክፍል ሦስት
## አደረጃጀትና አስተዳደር

**፯. የባለሥልጣኑ አቋም፡-**

፩/ ባለሥልጣኑ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተርና ለዳይሬክተሩ ተጠሪ የሆነ አንድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ይኖሩታል፣

፪/ ባለሥልጣኑ ለሥራው አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል።

15/ designate and specify prohibited, danger and restricted areas for marine transport in inland waterways in cooperation with other concerned governmental agencies;

16/ conduct and coordinate search and rescue operations for any vessel; investigate vessel accidents and prepare and issue accident reports;

17/ cause the establishment of marine transport institution vessel construction, maintenance and repair centers and other facilities related to vessel operations; inspect and determine their standards and award certificates of qualification;

18/ collect fees, rents and other charges payable for navigation and port services; to be submitted by the Ministry of finance and approved by the Council of Ministers.

19/ prepare and submit to the Ministry, draft Directives necessary for the implementation of this Proclamation and Regulations issued under this Proclamation; make such Directives known to concerned parties;

20/ enter into contracts, sue and be sued and submit disputes to arbitration; buy, sell, own or lease any kind of property as its activities require;

## Part Three
## Organization and Management

**7. Organization**

1/ The Authority shall have a Director General and a Deputy Director General accountable to him, both appointed by the Prime minister on the recommendation of the Minister.

2/ The Authority shall have the necessary staff.

## ፰. <u>የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር፡-</u>

ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሲሆን የባለሥልጣኑ ሥራና አስተዳደር በሚገባ ለመከናወኑ የበላይ ኃላፊ ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባር ይፈጽማል፡-

፩/ ባለሥልጣኑ በሕግ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት ገደብ ውስጥ ትእዛዞችን መረጃዎችንና የመሳሰሉትን እያዘጋጀ ማውጣት፤

፪/ የሥራውን ፕላንና ፕሮግራም፤ እንዲሁም ዓመታዊ ዝርዝር በጀት እያዘጋጀ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤

፫/ ብሔራዊም ሆነ አለም ዓቀፍ የማሪታይምና ትራንዚት ንግድ ዘርፍ የሚመለከት ማንኛቸውንም ጉዳይ እየተከታተለና እያጠና በየጊዜው ሪፖርትና ሐሳብ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤

፬/ የማሪታይም ዘርፍን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ መረጃዎችንና እስታትስቲኮችን በቋሚ ሁኔታ መሰብሰብ

፭/ ተጠሪነታቸው ለእርሱ የሆኑትን የባለሥልጣኑን ኃላፊዎች መርጦ ለሚኒስቴሩ በማቅረብ ያሾማል።

፮/ ሠራተኞችን በሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት መቅጠር፤ ማሳደግ፤ ማዛወር፤ ማስተዳደርና ከሥራ ማሰናበት፤

፯/ ለባለሥልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ኘሮግራም መሠረት የሚያስፈልገው ገንዘብ ወጭ ሆኖ እንዲከፈል ማድረግ፤

፰/ የባለሥልጣኑ ገቢና ወጭ፤ በቴክኒክ ረገድ የተፈጸሙትን ሥራና የሥራ እንቅስቃሴ የሚገልጽ የሒሳብና የሥራ መግለጫ ጽሑፍ በየሦስት ወር፤ እንዲሁም ዓመታዊ አጠቃላይ የሥራ ሪፖርትና በኦዲተር የተረጋገጠ የሒሳብ መግለጫ በየዓመቱ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤

፱/ ዋና ዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ከሥልጣኑና ከተግባሩ ለባለሥልጣኑ ሠራተኞች መወከል እና

፲/ ባለሥልጣኑ በሚከስበትም ሆነ በሚከሰስበት ማናቸውም ነገር ራሱ ወይም በነገረፈጁ አማካይነት የባለሥልጣኑ ወኪል ይሆናል።

## 8. Director General of the Authority

The Director General shall be the Chief Executive of the Authority, and shall in particular, carry out the following powers and duties:

1/ prepare and issue directives, information and other related matters within the legal scope of the Authority;

2/ prepare and submit to the Minister plans and programs as well as detailed annual budgets; and implement same where approved ;

3/ submit regular reports and proposals to the Minister on matters relating to national or international marine transport;

4/ collect regularly, information and statistics relating to marine transport;

5/ select and recommend to the Minister for appointment of officials of the Authority who are directly accountable to him

6/ employ, promote, transfer, administer or dismiss personnel allowances in accordance with the Civil Service law in force;

7/ effect payment in accordance with the approved annual budget and work program of the Authority;

8/ submit to the Minister audited quarterly financial and operational reports, as well as annual audited financial and comprehensive operational reports.

9/ The Director General may delegate part of his functions and powers to the employees of the Authority to the extent necessary for the efficient operations of the Authority;

10/ represent the Authority in person or through his attorney where it sues or sued;

**፱. ምክትል ዋና ዳይሬክተር፡-**

ዋናውን ዳይሬክተር ይረዳል፣ ዋናው ዳይሬክተር በሌለ ጊዜ ለዋናው ዳይሬክተር የተሰጡትን ሥራዎች ሁሉ ያከናውናል።

**ክፍል አራት**
**ልዩ ልዩ ጉዳዮች**

**፲. የገቢ ምንጭ፡-**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል፤

፩/ ከመንግሥት የሚመደብ በጀት

፪/ በባለሥልጣኑ የሚሰበሰብ ዓመታዊ ክፍያ፤ የአገልግሎት ዋጋ፤ የመመዝገቢያ ክፍያ፤ የንብረት ኪራይ ወይም ሽያጭ፤

፫/ ከማናቸውም ወገን የሚሰጥ የገንዘብ ዕርዳታ፤ እና ተግባሩን ሲያከናውን ከሚያገኘው ማናቸውም ሌላ ገቢ ።

**፲፩. ስለበጀትና የበጀት ዓመት፡-**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የባለሥልጣኑን በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል።

**፲፪. ስለሒሳብ መርማሪዎች፡-**

የባለሥልጣኑ የሒሳብ ሰነድ መዛግብትና ገንዘብ ነክ የሆነ ነገር ሁሉ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሾማቸው የሒሳብ መርማሪዎች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

**፲፫. ከግብር ነፃ ስለመሆን፡-**

፩/ በዓለም አቀፍ የባሕር ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ በተሰማሩ የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ድርጅት ሐመሮች ባለቤትነት ምክንያት በሚገኝ ገቢ ላይ ማናቸውም ዓይነት ግብር አይጠየቅም፤ ሆኖም ማናቸውም በባለሥልጣኑ የተመዘገበ ሐመር፤

ሀ/ ባለሥልጣኑ የሚያስከፍለውን ዓመታዊ የመርከብ ክፍያ፤

ለ/ የአገልግሎት ክፍያና፤

ሐ/ የሐመር መመዝገቢያና ክፍያ ይከፍላል፡

**10. Deputy Director General:-**

He shall assist the Director General carry out all powers and duties in his absence.

**Part Fore**
**Miscellaneous Provision**

**10. Source of Fund**

The fund of the Authority shall consist of:

1/ budget allocated by the Government;

2/ annual fees, service fees, registrations fees proceeds obtained from rents or sales of property;

3/ financial donations and income earned form services it renders.

**11. Budget and Budget year**

The Ministry of Finance and Economic Development shall prepare and submit the budget of the Authority to the Council of Ministers for Approval.

**12. Auditors**

The books of Account and all the financial affairs of the Authority shall be audited annually by the Auditor General or other auditors assigned by him.

**13. Tax Exemption**

1/ Any income that accrues to the Ethiopian Shipping Lines due to its ownership of vessels engaged in international marine transport services is exempt from any tax. However, any vessel registered by the Authority shall pay to it:

a). Annual charges levied by the Authority:

b). Service fees: and

c). Vessel registration fees

፪/ በኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ድርጅት ወይም በባለሥልጣኑ በተመዘገበ ሐመር ላይ ተቀጥሮ በዓለም አቀፍ የባሕር ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የተሰማራ ባሕረኛ የሚያገኘው ደሞዝ ማና ቸውም ዓይነት ግብር አይከፈልበትም።

## ፲፬. ክልከላ፡-

ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥራ መሠማራት የባሕር ማመላለሻ አገልግሎት ማካሔድ፤ የባሕር ማመላለሻ አገልግሎት መስጠት፣ የወደብ ዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ወኪልነት ሥራ ማካሄድ፣ ሐመር መግዛት፤ መሸጥ፤ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ወይም ከአገር ውጭ ማስወጣት፤ ወይም በሐመር መገልገል ወይም ባሕረኛ መሆን አይችልም።

## ፲፭. ስለትናንሽ ሐመሮች

ሚኒስትሩ የተለየ መመሪያ በማውጣት የዚህ አዋጅ ውሣኔዎች በትናንሽ ሐመሮች ላይ በሙሉ ወይም በከፊል ተፈጻሚ እንዳይሆኑ ለማድረግ ይችላል።

## ፲፮. አቤቱታ ስለማቅረብና ስለቅጣት

ሀ/ ሚኒስቴሩ በማሪታይም ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ባለኃብቶችና ሌሎች ግለሰቦች ከፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር ጋር በተያያዘ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ለሚቀርብለት የይግባኝ አቤቱታ ተቀብሎ ውሣኔ ይሰጣል።

ለ/ ይህን አዋጅና በአዋጁም መሠረት የወጡትን ደንቦች የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል።

## ፲፯. የተሻሻሉና የተሻሩ ሕጎች፡-

፩/ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፲፭ ሥር ወደብን በሚመለከት ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተሰጥቶ የነበረው ሥልጣንና ተግባር ተሽሮ ለባለሥልጣኑ ተላልፏል።

፪/ ትራንስፖርትን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯

ሀ/ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፭ ከፊደል /ሀ-ሐ/ እንዳለ ተሽረዋል።

2/ Employment income accruing to seafarers engaged on board seagoing regular marine transport service vessel registered by the Authority shall be exempt from taxes.

## 14. Prohibition

No person shall operate multi- modal or marine transport service or purchase, sell, import, export or use a marine transport service vessel, or be engaged as a seafarer on board any marine transport vessel unless he has obtained an authorization granted by the Authority.

## 15. Small Vessels

The Minister, by Directives, may waive the application in whole or in part of this proclamation to small vessels.

## 16. Appeal and Penalty

a) The Minister shall render the final decision on complaints submitted to it by investors on matters related to the issuance of license and supervision of their activities in the sector.

b) Any person who violates the provisions of this Proclamation and Regulation issued hereunder shall be punishable in accordance with the Penal Code.

## 17. Amendment and Repeal

1/ The powers and Duties given to the Ministry of Trade and Industry related to ports under the Definition of powers and duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No 471/2005 Article 15 is hereby repealed and given to the Authority

2/ with respect to Transport Proclamation no. 468/2005

a/ Article 7 Sub-Article 5 (a) trough (c) ;and

ለ/ በአንቀጽ ፳፫ ንዑስ ቁጥር /፩/ ስር ባሕረኛን በተመለከተ ለትራንስፖርት ባለሥልጣን የተሰጠው ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሽሮአል።

## ፲፰. ደንብና መመሪያ ስለማውጣት፡-

ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም፡-

ሀ/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስፈላጊ የሆኑትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል።

ለ/ ሚኒስቴሩ አስፈላጊ የሆኑትን መመር ያዎች ሊያወጣ ይችላል።

## ፲፱. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

b/ Powers given to the transport authority on matters related to seafarers under Article 23 (1), are all hereby repealed

## 18. Regulations and Directives

For the proper implementation of this Proclamation

a. The council of Ministers may issue the necessary regulation;

b. The Ministry may issue the necessary Directives

## 19. Effective Date

This Proclamation shall come into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 4th day of September, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**